እስከዛሬ የሰው ጉበዝ አይቻለሁ
እስከዛሬ የሰው ብርቱ አይቻለሁ
እስከዛሬ የሰው ሐያል አይቻለሁ
እስከዛሬ የሰው ጀግና አይቻለሁ

እንዳንተ ያለ ግን ጉበዝ የለም
እንዳንተ ያለ ግን ብርቱ የለም
እንዳንተ ያለ ግን ሐያል የለም
እንዳንተ ያለ ግን ጀግና የለም

በሐዘኔ በችግሬ ጊዜ
ጀርባውን ያላዞረው
ኢየሱስ ነው ኢየሱስ ነው
እስከዛሬ በራሴ ጉልበት አልዋልኩኝም
እስከዛሬ በራሴ ብቃት አላደርኩኝም
ባለውለታዬ (2) ገበናዬን ሸፋኜ ኤሂሂ
ባለውለታዬ (2) ምስጥሬን ጠባቂዬ





EECFC-NC

ክብር የተሞላ <u>እግዚአብሄር ሆይ</u> (2)
ገናና ጌታ ነህ <u>እግዚአብሄር ሆይ</u> (2)
የማትለዋወጥ <u>እግዚአብሄር ሆይ</u> (2)
ፍቅርህ የማያረጅ <u>እግዚአብሄር ሆይ</u> (2)
ትኖራለህ ዛሬም ለዘላለም
እኩያ የለህ ወደርም የለህ
የሚመስልህ የለም ለዘላለም
የማትለዋወጥ አንተ ያው አንተ ነህ
እግዚአብሄርን አመስግኑ (2)
እግዚአብሄርን አመስግኑ (3) ...

ቸርነቱን በህይወታችሁ ያያችሁ እግ/ን
አመስግኑ (2)
በሃይል ሳይሆን በፍቅሩ የገዛችሁ እግ/ን
አመስግኑ
በምህረቱ የቆማችሁ እስከዛሬእግ/ን አመስግኑ
(2)
እግዚአብሄርን አመስግኑት በዝማሬ (2)
እግዚአብሄርን አመስግኑ (2)
እግዚአብሄርን አመስግኑ (3)
ታላቅ ስሙን ደግሞ ጥሩት (3)
ዘምሩለት ዘምሩለት
ስገዱለት ስገዱለት

የመከራን የጭንቅ ዘመን አሳልፎ እግ/ን
አመስግኑ
ጨለማውን ሌሊቱንም ሁሉ ገፎ እግ/ን
አመስግኑ
እንደዋላ ያስኬዳችሁ በከፍታ እግ/ን
አመስግኑ (2)

እግዚአብሄርን አመስግኑ (2)
እግዚአብሄርን አመስግኑ (3)
ታላቅ ስሙን ደግሞ ጥሩት (3)
ዘምሩለት ዘምሩለት
ስገዱለት ስገዱለት

ተንቃችሁ በሰዎች ዘንድ ተረስታችሁ እግ/ን
አመስግኑ
ስትገፉ ዙሪያችሁን ተከባችሁ እግ/ን
አመስግኑ (2)
እግዚአብሄርን ግን ከማደሪያው ያነሳችሁ
እግ/ን አመስግኑ (2)

እግዚአብሄርን አመስግኑ (2)
እግዚአብሄርን አመስግኑ (3)
ታላቅ ስሙን ደግሞ ጥሩት (3)
ዘምሩለት ዘምሩለት
ስገዱለት ስገዱለት